የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት ሕብረት

Union of Ethiopian Provinces

www.ethiopianhibret.com

ethiopianhibret@gmail.com

6/30/2018

# <u>የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት ሕብረት መግለጫ</u>

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከብዙ አገራት መፈጠር በፊት መንግስታዊ ሥርዓት መስርታ በነጻነት ለረጅም ዘመናት የኖረች  ሀገር ከመሆኗም በላይ የሰው ዘር የፈለቀባት ምድር ናት።በየጊዜው የመጡባትን ወራሪ ጠላቶች በዜጎቿ ጠንካራ አንድነትና ከፍተኛ  መስዋእትነት አሳፍራ መልሳለች።በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ የተገነባው የሕዝብ ጠንካራ አገራዊ መንፈስ ለተገኙት ድሎች ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ምንም ጥርጥር የለውም።  አንድነትን መሰረት ባደረገና ከዚህም በመነጨ ብሔራዊ ስሜት የተገነባው ሕዝባዊ ሃይል በአድዋ ያገኘው ድል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የጥቁር ህዝብ ሁሉ ድል ከመሆኑም በላይ በቅኝ ግዛት ይማቅቁ ለነበሩ  የእስያና የደቡብ አሜሪካ ሕዝቦች የነጻነት ፋና ወጊ በመሆን ለትግላቸው የብርታት ምሳሌ ሆኗል። ወደፊትም በዚህ ታላቅ ምሳሌነት ይኖራል። ከዚያም ወዲህ የእናት ሀገሩን ዳር ደንበር ለማስከበር በጋራ  የከፈለው መስዋዕትነት የአንድነታችን ምሳሌና ውጤት ነው።

ሀገራችን ለአስተዳደር በሚያመቹ መልኩ የተፍጥሮ መልክዓምድር አቀማመጥ በተዋቀረ የክፍለሀር አወቃቀር በምትመራበት ዘመን በርካታ ማህበረሰብ ክፍሎች በመንግሥትም ተቋም ሆነ በግል ሥራ ተሰማርተው በፈለጉት ክፍለሀገር ባይታወርነት ሳይሰማቸው ይኖሩ እንደነበረ የሚታወቅ ነው። አሁንም በዚያው ተወልደው የሚኖሩ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። በመሆኑም፣ በዚህ የሕዝብ አብሮነትና መስተጋብር በርካታ የባህልና የሥራ ልምድ ከመካፈሉ በተጨማሪ በጋብቻ ሰንሰለት ተሳስሮ በመዋለድ ከአገር ልጅነትም በላይ በቤተሰብነት የእትብት ትስስር የማይላቀቅ ዝምድናን አትርፈዋል።

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የጋራ መገለጫና መከበሪያ የሆነውን ኢትዮጵዊነትን እንደ ዋነኛ ጠላት በመቁጠር ህዝብ በቋንቋና በጎሳ እየተነጠለ በጠባብ ክልል ውስጥ እንዲኖር ከተፈረደበት 27 ዓመታት አለፈው። በዚህም የተነሳ ብዙ ዜጎች በሰላም አብረው እንዳይኖሩ እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ ሆኗል። በዚህም የጥፋት ጎዳና ብዙ የንጹሃን ዜጎች ህይወት ሲጠፋ አያሌ ንብረትና የታሪክ ቅርሶችም ወድመዋል።  ላለፉት 27 ዓመታት በህወሀት/ኢህአዴግ እኩይ ስራ በጋራ የተገኙትና የተገነቡት በርካታ ድሎች ተዘንግተው እንሆ ዛሬ ካለንበት የተመሰቃቀለ አሳፋሪ ደረጃ ላይ ደርሰናል።

ብዙ ህዝብና የቆዳ ስፋት ያላቸው ትልልቅ ሀገሮችም ሆኑ ትንንሽ ሀገሮች በዛሬው ዓለም መንግሥት በፈጠረው የዘርና የቋንቋ ልዩነት ህዝባቸውን ከልለው የሚኖሩ የሉም። እንደ ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋና የተለያዩ ባህል ያላቸው የአፍሪካ ሀገሮች መኖራቸውን ብናወቅም ህዝባቸውን በዚሁ ረገድ ከፋፍለው የሚያስተዳድሩ የሉም። የሞከሩትም ከብዙ ጉዳት በኋላ ትምህርት ቀስመው የጎሳ  ተኮር ፖለቲካና አደረጃጀትን በሕገ መንግሥታቸው ከልክለዋል። በአጠቃላይ የዓለም ሀገሮች ህዝባቸውን የሚያስተዳድሩት ለቁጥጥና ለአሠራር በሚያመች፣ በተፈጥሮ አቀማመጥ፣ የሕዝብን አሰፋፈር ከግንዛቤ በማስገባትና  ለኤኮኖሚያዊ ሀብት ክንዋኔ አመችነት መሰረት በማድረግ ነው። ህወሀት / ኢህአዴግ ለተዛባና ጥቂቶችን የበላይ ላደረገ አስተዳደር ያመቸው ዘንድ ሀገራችንን በቋንቋ በመከፋፈል ብዙ ሺህ ቤተሰብ ከሚኖርበት አካባቢ እንደ

ባይታወር እየተቆጠረ ህይወቱ ጠፍቷል፣ ንብረቱ ወድሟል፣ ተፈናቅሏል።ይህም አገዛዙ የፈጠረው የአስተዳደር ክልል የኢትዮጵያን አንድነት እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ቦርቡሮታል፣ የህዝቡንም አድገት ጎድቶታል፣ ከአሁኑ ካልተቀጨ ለወደፊትም መጥፎ መድረሻ ላይ ሀገራችንን ሊጥል እንደሚችል ሊታሰብ ይገባዋል።

በሀገራችን የተፈጠረውን ችግር ለማስወገድና ህዝባችን ላይ የተደቀነውን ፈተና ለመቅረፍ ብሎም ወደፊት ሊደርስ የሚችለውን ከፍተኛ አደጋ በቅድሚያ  ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ፣ የኢትዮጵያ ክፍላተሃገር ሕብረት በቀድሞ ክፍላተሃገር ተወላጆች ተመስርቷል። ከሕብረቱ አላማዎችና ግቦች አንደኛው አሁን ያለው በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የክልል አስተዳደር  በተሻሻለና ኑዋሪውን ባሳተፈ ዴሞክራሲያዊ መልክ በተዋቀረ በነባሩ የህዝብ ታሪካዊ አሰፋፈርና የመሬት የቆዳ ስፋት እንዲዋቀር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ነው። ይህንን ዓላማውን ብዙዎች የሚጋሩት ሲሆን ዛሬ በሀገራችን እየተከሰቱ ላሉት ችግሮች መፍትሔ እንደሆነ ይታመንበታል። በአሁኑ ሰዓት የተፈጠረውን የለውጥ ተስፋ በመጠቀም አላማውን ለማሳካት እጅግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግም ላይ ነው።

የኢትዮጵያ ክፍላተሃገር ሕብረት አላማውን ከግብ ለማድረስ ከማንኛውም ሀገር ወዳድ ድርጅት ጋር ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን እንገልጻለን። ከዚህም በተጨማሪ፣ በሀገራችን የተፈጠረውን ተስፋ ሰጭ ሁኔታ በመጠቀም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በጋራ ለማሻሻልና ለመለወጥ በሚደረገው ጥረት መሰባሰብ አስፈላጊ እንደሆነ በማመን ሀገር ወዳድ ሀይሎች ሁሉ በመሰባሰብ አንድ ጠንካራ ብሄራዊ አማራጭ ፈጥረን በአንድነት እንድንታገል ጥሪ እናደርጋለን፣

- በጠቅላይ ሚኒስትር ዶር አብይ የሚመራው የለውጥ ፈላጊ ክንፍ የሚወስዳቸውን  ተስፋ ሰጭ እርምጃዎችና ኢትዮጵያዊነትን፣ ሰላምንና  ፍቅርን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶችን እንደግፋለን።
- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶር አብይ አህመድን ለመደገፍ በተደረገው ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ወቅት በሽብርተኞች የተፈጸመውን የፈንጅ ጥቃት እናወግዛለን፤
- በንጹሃን ወገኖቻችንም ላይ በደረሰው የሞትና የመቁሰል ጉዳት ልባዊ ሀዘናችንን እየገለጽን፣ ወንጀለኞ ተጣርተው በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን።
- የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ ለመቅጨትና የወያኔን የበላይነት እንደገና ለመመለስ የሚካሄደውን ደባ በጥብቅ እንቃወማለን፣
- በሀገራችን የዜግነት(የግለሰብ) መብት የሚከበርበት ፍትሃዊ ተቋምን መመስረትና ሕገመንግሥት መንደፉ ጉዳይ ቅድሚያ እንዲሰጠው እናሳስባለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር! የኢትዮጵያ
ክፍላተሃገር ህብረት